# መጽሐፈ ሰዓታት በግዕዝና በአማርኛ

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሰዳዴሆም ለአጋንንት ስድዶሙ እግዚኦ ለአጋንንት እምየማንነ ወእምጸጋምነ ወእምዛቲ መካንነ ይርኃቁ እመኔነ ለእለ ይጸብእዋ ለነፍስነ።

አቤቱ አጋንንትን የምታሳድዳቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከግራ ከቀኛችን ከዚችም ቦታችን ከኛም ይርቁ ዘንድ ሰውነታችንን የሚዋጓት አጋንንትን አሳዳቸው

ከመዝ መሀሩነ ሐዋርያት በሲኖዶሶሙ።

ሐዋርያትም (በጉባኤ) በመጽሐፋቸው እንዲህ አስተምረውናል

ቀሳውስት ጽፉቀ እንዘ ይጼልዩ በዛቲ ሰዓት
መንፈቀ ሌሊት ተንሢአከ ተሐፂበከ በማይ ጸሊ።
ወእመሰ ብእስቲከ መሃይምንት ፪ክሙ ጸልዩ።

በዚች ሰዓት ቀሳውስት ባንድነት ሲጸልዩ በመንፈቀ ሌሊት ተነሥተህ በውሃ ታጥበህ ጸልይ። ሚስትህም በወንጌል ያመነች ብትሆን ሁለታችሁም ጸልዩ።

ወንፋህ ውስተ እደዊከ ወተሐጸብ በምራቅ ዘይወጽእ እምአፉከ። ወትከውን ንጹሐ እምርእስከ እስከ እገሪከ።

በእጆችህም እፍ ብለህ ከአፍህ በሚወጣ ምራቅ ታጠብ። ከራስህ እስከ እግርህ ንጹሕ ትሆናለህ።

ዝውእቱ አምኃ መንፈስ ቅዱስ።

ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ እጅ መንሻ ነው (ብለው አስተምረውናል)።

በዛቲ ሰዓት ኵሉ ፍጥረት ይፃምው ለስብሖቱ ለእግዚአብሔር።

በዚችም ሰዓትም ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይተጋሉ።

ወከዋክብት አትክልት ዕፅ ወማያት ይቀውሙ ሰዓተ።

በዚችም ሰዓትም ከዋክብት ዕጽዋት ውሆችም ጸጥ ብለው ይቆማሉ።

ወኵሎሙ ሠራዊት መላእክት ይትቀንዩ ዘንተ ሰዓተ ምስለ ነፍሳተ ጻድቃን እንዘ ይሴብሑ ወይዜምሩ ለእግዚአብሔር ሃሌ ሉያ፣ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ።

በዚችም ሰዓትም የመላእክት ሠራዊት (ወገን) ሁሉ ከጻድቃን ነፍሳት ጋራ ቅድመ ዓለም የነበርክ ዓለምን አሳለፊህ የምትኖር ብለው እያመሰገኑ ለእግዚአብሔር ይገዛሉ።

ስምዕዎ ለሐዋርያት ቃሎሙ።

እንዲህ ብለው ያስተማሩትን የሐዋርያት ቃል ስሙ።

ሃሌ ሃሌ ፣ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ አአትብ ወእትነሣእ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

ቅድመ ዓለም በነበረ ዓለምን አሳልፎ በሚኖር በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተነስቼ አማትባለሁ።

፫ተ አስማተ ነሢእየ እትመረጐዝ። እመኒ ወደቁ እትንሣእ። ወእመኒ ሖርኩ ውስተ ጽልመት እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ በእግዚአብሔር ተወከልኩ

የሦስቱን ስም ይዤ እመረኰዛለሁ። ብወድቅም እነሣለሁ። ወደ ጨለማም ብሄድ እግዚአብሔር ያበራልኛል በእግዚአብሔር አምኛለሁና።

መስተብቍዕ□

□

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘገብረ ዓቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ። ወይትባረክ ስመ ስብሓቲሁ ቅዱስ።

ብቻውን ታላላቁን ተአምራት ያደረገ የእስራኤል (ፈጣሪ) እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። የከበረ የጌትነቱም ስም ይክበር ይመስገን።

ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኵሎ ለይኩን ለይኩን።

ጌትነቱም በዓለሙ ሁሉን የመላ ይሁን ይኸውም ይሁን ይደረግ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅዳሳተ ስብሓቲከ።

ጽኑዕ ክቡር ልዩ ፍጹም አቸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይ በምድር የመላ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወይሄሉ እስከ ለዓለም።

ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይሴባሕ እምት ጉሃን ወይትቄደስ እምቅዱሳን።

ክቡራን ትጉሃን የሆኑ መላእክት የሚያመሰግኑት እግዚ አብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይፈርህዎ ኪሩቤ ል ወእምግርማሁ ይርዕዱ ሱራፌል።

ኪሩቤል የሚፈሩት ከግርማው የተነሳ ሱራፌል የሚንቀ ጠቀጡለትእግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይመይጦ ለመብ ረቅ ወያጽነዖ ለነጐድጓድ።

መብረቅን ከቁጣ የሚመልሰው ነጐድጓድን ጸጥ የሚያ ደርገው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይክዕዎ ለጽል መት ፍናወ ሰርክ ወይመይጦ ለብርሃነ መንገለ መስዕ

በሠርክ ጊዜ ጨለማን የሚያፈሰው (የሚያመጣው) ብር ሃንን ወደ መስዕ የሚመልሰው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአኮንኖ መዓልተ ለፀሐይ ከመ ያበርህ ለነ ውስተ ጠፈረ ሰማይ።

በጠፈር ሁኖ ያበራልን ዘንድ ፀሐይን በመዓልት ያሰለጠ ነው ያስገዛው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአኮነንኖሙ ለወ ርኅ ወለከዋክብት ከመ ይሰልጡ ግብሮሙ በሌሊት

ጨረቃ ከዋክብትንም ሥራቸውን በሌሊት ዘንድ ያሰለ ጠናቸው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይሬስዮሙ ለመ ላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት።

የሚያገለግሉት መላእክትንም ከእሳት ከነፋስ የፈጠራቸ ው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘረበቦ ለሰማይ ከ መሐይምት ወአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ።

ሰማይን እንደ ድንኳን የዘረጋው ምድርንም በውኃ ላይ ያጸናት እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለአዳም በዘዚአሁ አርአያ ወአምሳል።

አዳምን በሱ አምሳል የፈጠረው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነ ው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘምስለ ኖኅ ኪዳ ነ ዘአቀመ።

ከኖኅ ጋር መሐላውን ያጸና እግዚአብሔር ፅኑዕ ነው ክቡር ነው ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘሠርዐ ለአብርሃ ም ወመሐለ ለይሰሐቅ ወአቀመ ስምዐ ለያዕቆብ።

ለያዕቆብ የመሰከረ ለይስሐቅ ለአብርሃም ሕግን የሠራ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘምስለ ዮሴፍ ተ ሰይጠ ከመ ይኩን ሲሳየ ለሕዝብ።

ለወገኖቹ ምግብ ይሆን ዘንድ (ወገኖቹን ይመግብ) ዘንድ እንደ ዮሴፍ በዮሴፍ አምሳል የተሸጠ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስእግዚአብሔር ዘወሀበ ሕገ ለሙሴ

ለሙሴ ሕግን የሰጠ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘቀደሰ ክሕነቶ ለ አሮን።

የአሮንን ክህነት ያከበረ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘቀብዖ ለዳዊት ቅብዓ ትንቢት ወመንግሥት።

ሀብተ ትንቢት ሀብተ መንግሥት የሚሆን ቅብዕን ቀብቶ ዳዊትን ያነገሠ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበነቢያት አስተ ንፈሰ ከመ ያስምዕ ቃሎ ለሕዝብ።

ለወገኖቹ ቃሉን ያሰማ ዘንድ በነቢያት አድሮ ያናገረ እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይሴብሕዎ መላ እክት ወያአኵትዎ ሥልጣናት።

መላእክት የሚያመሰግኑት ሥልጣናት የሚያገለግሉት እግዚአብሔር ፅኑዕ ክቡር ልዩ ነው

ግነዩ ለእግዚአብሔር ወጸውዑ ስሞ ሃሌ ሉያ ወንግር ዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ።

ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለእግዚ አብሔር እየተገዛችሁ ስሙን ጥሩ (አመስግኑ) ለአሕዛ ብም ሥራውን ንገሯቸው

| | |
|---|---|
| ግነዩ ለእግዚአብሔር እሰመ ኄር ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለእግዚአብሔር ተገዙ ቸር ነውና ቸርነቱ ለዘለዓለም ስለሆነ። |
| ንግሩ ቤተ እስራኤል ከመ ኄር ሃሌ ሉያ ከመ ለዓለም ምሕረቱ። | የእስራኤል ወገኖች ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔር ቸርነውና ቸርነቱ ለዘለዓለም እንደሆነ ንገሩ። |
| ንገሩ ቤተ አሮን ከመ ኄር ሃሌ ሉያ ከመ ለዓለም ምሕረቱ። | የአሮን ወገኖች ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔር ቸር ነውና ቸርነቱ ለዘለዓለም እንደሆነ ንገሩ። |
| ንገሩ ኵልክሙ እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር ከመ ኄር ሃሌ ሉያ ከመ ለዓለም ምሕረቱ። | እግዚአብሔር የምትፈሩ ሁላችሁ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ጌታ ቸር ነውና ቸርነቱ ለዘለዓለም እንደሆነ ንገሩ። |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለመኰንነ ጽድቅ ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር እውነት ለሚፈርድ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለንጉሠ ርትዕ ሃሌ ሉያ እሰመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለእውነተኛ ንጉሥ ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለአኃዜ ዓለም ሃሌ ሉያ እሰመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ዓለምን ጨብጦ ለያዘ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና. |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለብርሃነ ቅዱሳን ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለቅዱሳን ብርሃን ለሚሆን ለእግዚአብሔር ተገዙ ቸርነቱ ለዘለዓለም ነውና |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለአክሊለ ንጹሐን ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር የንጹሐን ክብራቸው ዘውዳቸው ለሚሆን ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለእግዚአብሔር ለዓርከ ብፁዓን ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለደጋጎቹ ወዳጅ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለአምላከ አማልክት ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለአማልእክት ፈጣሪ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለእግዘዚእ አጋዕዝት ሃሌ ሉያ እሰመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ጌቶቹን ለሚገዛ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ግነዩ ለአምላከ ሰማይ ሃሌ ሉያ እስመ ለዓለም ምሕረቱ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ሰማይንለፈጠረ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይቅርታው ለዘለዓለም ነውና። |
| ምሕረተከ እሴብሕ እግዚኦ ለዓለም ሃሌ ሉያ እገኒ ለከ እግዚኦ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አቤቱ ቸርነትህን ለዘላለሙ እናገራለሁ አቤቱ ላንተም እገዛለሁ። |
| ምሕረትከ ወጽድቅከ ዘልፈ ይረከባኒ ሃሌ ሉያ እገኒ ለከ እግዚኦ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር ይቅርታህ ቸርነትህ ዘወትር ያግኙኝ ይደረጉልኝ አቤቱ ላንተም እገዛለሁ። |
| እስመ መሐሪ አንተ እግዘእ ወመተሣህል ሃሌ ሉያ እገኒ ለከ እግዚኦ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አቤቱ አንተ ቸር ይቅር ባይ ነህና ላንተ እገዛለሁ |

| | |
|---|---|
| ርኁቀ መዓት ወብዙኃ ምሕረተ ወጻድቅ ሃሌ ሉያ እገኒ ለከ እግዚኦ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር መዓትህ የራቀ ይቅርታህ የበዛ እውነተኛ ነህና አቤቱ ላንተ እገዛለሁ። |
| እገኒ ለከ እግዚኦ በኵሉ ልብየ ሃሌ ሉያ ወእነግር ኵሎ ስብሓቲከ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አቤቱ በፍጹም ልቦናዬ ላንተ እገዛለሁ ምሥጋናህንም እናገራለሁ |
| እገኒ ለከ እግዚኦ በኵሉ ልብየ አምላኪየ ሃሌ ሉያ እሰመ ስማዕከኒ ኵሎ ቃለ አፉየ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር ፈጣሪዬ ልመናዬን ሁሉ ሰምተኸኛልና አቤቱ በፍጹም ልቡናዬ ላንተ እገዛለሁ |
| እገኒ ለከ እግዚኦ እገኒ ለከ ሃሌ ሉያ እገኒ ለከ ወእጼውዕ ስመከ። | ቅድመ ዓለም የነበርህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አቤቱ ፈጽሜ ላንተ እገዛለሁ ስምህንም እጠራለሁ። |
| እገኒ በአፉየ ለእግዚአብሔር ፈድፋደ ሃሌ ሉያ ወእሴብሖ በውስተ ሕዝብ ክቡድ። | ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔርን ባንደበቴ እለምናለሁ በብዙ ሕዝብም መካከል አመሰግነዋለሁ። |
| ስብሓት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሃሌ ሉያ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት። | ቅድመ ዓለም ለነበሩ ዓለምን አሳልፈው ለሚኖሩ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው በየሰዓቱ ምሥጋና ይገባቸዋል |
| ስብሓት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሃሌ ሉያ በኵሉ አዝማን ወበኵሉ ዓመታት። | ቅድመ ዓለም ለነበሩ ዓለምን አሳልፈው ለሚኖሩ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ በያመቱ በየዘመኑ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል |
| ስብሓት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሃሌ ሉያ በቅድስት ቤተ ክርስትያን። | ቅድመ ዓለም ለነበሩ ዓለምን አሳልፈው ለሚኖሩ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ በከበረች ቤተ ክርስትያን ምስጋና ይገባቸዋል |
| ለዓለም ወለዓለም ሃሌ ሉያ ለትውልድ ትውልድ ሎቱ ይደሉ ሰጊድ። | ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለሱ በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም በልጅ ልጅም ስግደት |
| እዌድሰኪ ኦ ድንግል መልእተ ውዳሴ መጠነ ይክል አፉየ አስተበፅዕ ዕበየኪ። | ክብር ምስጋና የተመላሽ ድንግል ሆይ አንደበቴ የሚችለውን ያህል አንቺን እያመሰገንሁ ገናንነትሽን አደንቃለሁ። |
| ልሳነ ኪሩቤል ኢያክል አበጽሖ ውዳሴኪ ወአፈ ሱራፌል ኢይፌጽም ነጊረ ዕበየኪ ማርያም። | እመቤታችን ሆይ የኪሩቤል አንደበት ምሥጋናሽን ማድረስ አይቻለውም የሱራፌል አንደበት ገናንትሽን ተናግሮ አይፈጽመውም። |
| ትትሌዓሊ እምአድባር ወእመ አርእስተ አውግር ነዋኀት ናዓብየኪ ኦ ቡርክት ማኅፈደ መለኮተ ማርያም | ከታላላቆቹ ተራሮች ማለት ከደጋጎቹ አባቶችሽ ትበልጫለሽ የመለኮት ማደሪያው ክብርት እመቤታችን ሆይ እናከብርሻለን እናገንሻለን። |
| ፅበተ ከርሥኪ ሰፍሐ እመርኅበ ማይ ወጸዳልኪ አብርሀ እምብርሃነ ፀሐይ። | የማኅፀንሽ ጽበት ከሰማይ ስፋት ይልቅ የበዛ ነው ብሩህነትሽም ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ የበለጠ ነው። |
| አስከሬነ ወርቅ ጽሩይ መዝገበ ባሕርይ ቡርክት አንቲ ማርያም። | ክብርት እመቤታችን የጠራ የወርቅ ሳጥን የእንቁ ማኖሪያ አንቺ ነሽ |

**ውድስት** አንቲ በአፈ ነብያት ወስብሕት በሐዋርያት አክሊላ በረከቱ ለያዕቆብ ወትምክህተ ቤቱ ለእስራኤል።

**ሥርፀ** መንግሥት ዘእምሥርወ ዕሴይ ወጽጌ ንጽሕት ዘእምጕንደ ዳዊት ወብኪ ይትሜዓዙ ኲሎሙ ቅዱሳን።

**ንሰግድ** ለኪ ኦ ንግሥት ወናንቀዓዱ ኀበ ወልድኪ አ ኃዜ ዓለም ስፍሒ እዴኪ ወባርኪ ላዕሌነ ለለ፩፩ ለ አግብርትኪ።

**እግዚኦ** መሐረነ ክርስቶስ ፲ተ፤ ወ፪ተ፤ ጊዜ

**በነቢያት** በሐዋርያት እንደበት የተመሰገንሽ የያዕቆብ የበረከቱ ዘውድ የእስራኤል ወገን መመኪያ አንቺ ነሽ

**ከዕሤይ** ሥር የተገኘሽ የመንግሥት ቡቃያ ከዳዊት ግንድ የ ተገኘሽ ቅዱሳን የሚቀቡሽ (የሚከብሩብሽ) ንጽሕት አበባ አንቺ ነሽ

ንግሥት ሆይ ላንቺ እንሰግዳለን ዓለሙን ጨብጦ ወደያዘ ልጅሽም እንለምናለንና እያነዳንዳችን እኛ አገልጋዮችሽን እጅሽን ዘርግተሽ ባርኪን

አሥራ ሁለት ጊዜ አቤቱ **ክርስቶስ** ይቅር በለን እንበል